በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

**የሰ/መ/ቁ.** 201128

ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች-** ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ- ጠበቃ ሰለሞን ረዳ

**ተጠሪ-** ወ/ሮ ቢቂልቱ በየነ- ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ የፍርድ ባለመብት በመሆን የፍርድ ባለዕዳ በሆኑት በአመልካች እና ሌሎች ሁለት ግለሰቦች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64593 ላይ በቀን 10/08/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

የአፈፃፀም አቤቱታዉ የቀረበለት ፍርድ ቤት አከራካሪው ይዞታ በገፈርሳ ቡራዩ ቀበሌ አስተዳደር አማካኝነት ተለክቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ስፋቱ 842.8 ካ.ሜ እንደሆነ፤ ተጠሪ ደግሞ በክሳቸው ላይ የጠቀሱት የይዞታ መጠን 660 ካ.ሜ ስለመሆኑ መገንዘቡን ጠቅሶ የፍርድ ባለእዳዎች በዚሁ መጠን ለአመልካች እንዲያስረክቡ፣ ከዚህ ውጪ የሚተርፍ ይዞታ ካለና ባለመብት ካልተገኘ የከተማው አስተዳደር ወደ መሬት ባንክ እንዲያስገባ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የይግባኝ አቤቱታ በማጣመር ከመረመረ በኋላ ትርፍ ነው የተባለውን መሬት የቡራዩ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ይዉሰድ መባሉ ስህተት ነው፤

ተጠሪ በአራቱም አቅጣጫ አዋሳኝ ጠቅሰው ያቀረቡትን ክስ መጠኑ በባለሞያ እንዲጣራ ከማዘዝ ውጪ ትክክለኛውን መጠን አልጠቀሱም ሊባል አይገባም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች በቅደም ተከተል ቢያቀርቡም ተቀባይት አላገኙም፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 12/05/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በአጭሩ ክርክር ያስነሳውና ተጠሪ እንዲረከቡት የተወሰነላቸው ይዞታ መጠን 660 ካ.ሜ ሆኖ እያለ ከዚህ መጠን በላይ አመልካች በውርስ ያገኙሁትን ይዞታ በማጠቃለል በአፈፃፀም እንዲረከቡ መወሰኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአከራካሪው ይዞታ አፈፃፀም ፍርዱን የተከተለ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ከፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ህግ አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በቀን 22/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን ውሳኔ ሲሰጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ስፋት ያላጣራ ሲሆን በደፈናው የተጠሪ ይዞታ ላይ የተፈጠረው ሁከት ተወግዶ የፍርድ ባለእዳዎች የሰሩትን አጥር አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁ ወሰነ እንጂ የይዞታውን መጠን አልገለፀም፤ በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረብቡኩበት ይዞታ መጠኑ 1300 ካ.ሜ የነበረ ሲሆን መንግስት በይዞታው ላይ መንገድ በማውጣቱ መጠኑ ቀንሷል፤ አመልካች በዚህ አካባቢ ምንም አይነት መሬት የላቸውም፤ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዋሳኙ የተጠቀሰውን መሬት በአፈፃፀም እንድረከብ ትዕዛዝ መስጠቱ ስህተት ስለሌለው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክራለች፡፡ አመልችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለአፈፃፀሙ ምክንያት ለሆነዉ ዉሳኔ መነሻ የሆነዉን ክስ ተጠሪ ሲያቀርቡ አዋሳኞቹንም በአራት አቅጣጫ በመጥቀስ ሲሆን ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ ይዘትም አዋሳኙ ከተጠቀሰዉ ይዞታ ዉስጥ የሚገኘዉ ይዞታ የተጠሪ በመሆኑ አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ተከሳሾች ሁከት አስወግዶ በቦታዉ ላይ ያጠሩትን አጥር ያፍርሱ የሚል ስለመሆኑ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠዉ የፍርድ ሃተታ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ወይም ለአፈፃፀሙ መነሻ

የሆነዉ ፍርድ ካረፈበት ይዞታ አጠገብ አዋሳኝ ይዞታ ያላቸዉ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ለፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔም ይሄዉ ነዉ፡፡

ፍርድ እንዲያስፈጽም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ፣ ማለትም በፍርዱ ላይ በተመለከተዉ ላይ ሳይጨምር ወይም ሳይቀንስ፣ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ዳኝነት ያላግባብ የተወሰደ ንብረት ወይም ሀብት እንዲመለስ ወይም ገንዘብ እንዲከፈል ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ በሚሰጥ ዉሳኔ የፍርድ ባለመብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለዉ በተሰጠ ፍርድ መሠረት የተፈጸመለት እንደሆነ ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ጉዳይ የሚፈጀዉ ጊዜ እንደ የጉዳዩ ዓይነትና ባህርይ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም፣ ክስ ከቀረበበት ጀምሮ እስከ ዉሳኔ ድረስ ያለዉ ሂደት የተወሰነ ጊዜ መዉሰዱ አይቀሬ ነዉ፡፡ በዚህም ሂደት የፍርድ ቤት ብሎም የተከራካሪ ወገኖች ጊዜ ይባክናል፤ ወጪና ድካም ይኖራል፡፡ ስለሆነም ፍርድን እንደ ፍርዱ ማስፈጸም ይህን ሂደት በማለፍ የተሰጠ ፍርድ ፍሬ አልባ እንዳይሆን የማድረግ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል ከመሆኑም በላይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ፍርድ ተፈፃሚነቱ ተገማች እንዲሆን ያስችላል፡፡ የፍት/ብ/ሥነ ሥርዓት ህጋችን ሰባተኛ መጽሐፍ ከአንቀጽ 371 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎቹ የፍርድ አፈፃፀም የሚመራበትን ሥነ-ሥርዓት ይደነግጋል፡፡ የፍርድ አፈፃፀም የቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚህ የመጽሐፉ ክፍል የተዘረጋዉን ስርዓት በመከተል ድንጋጌዎቹን እንደየአግባብነታቸዉ ተግባራዊ በማድረግ አፈፃፀሙን በመምራት እንደ ፍርዱ የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ለአፈፃፀሙ መነሻ ለሆነዉ ዉሳኔ ምክንያት በሆነዉ ክስ ተጠሪ የጠቀሱት የይዞታ መጠን 660 ካ/ሜትር የሚል ቢሆንም የተሰጠዉ ዉሳኔ በክሱ ላይ አዋሳኞቹ የተጠቀሰዉ ይዞታ የተጠሪ መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ በአዋሳኙ የተመለከተዉ የይዞታ መጠን ከ660 ካ/ሜትር በላይ 842.8 ካ/ሜትር መሆኑ ቀሪዉ ይዞታ ማለትም 182 ካ/ሜትር ፍርድ ያላላረፈበት ነዉ ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባዉ ይዞታዉ ተለክቶ በታወቀዉ መጠን እና በተጠሪ ክስ ላይ በተጠቀሰዉ መጠን መካከል ልዩነት በመፈጠሩ ብቻ 182 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ፍርድ አላረፈም በማለት መቀነሱ የፍርዱን ትክክለኛ ይዘት ያላገናዘበ ሲሆን፣ በአንፃሩ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ በማረም በፍርዱ ላይ አዋሳኙ የተጠቀሰዉ ይዞታ ለተጠሪ እንዲፈጸም በማለት ዉሳኔ መስጠቱ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ይህንኑ ዉሳኔ በማጽናት የሰጡት ትዕዛዝ የፍርድ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረታዊ መርህን ለአፈፃፀሙ ምክንያት ከሆነዉ ዉሳኔ ጋር በማገናዘብ የተሰጠ እና በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

1. በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39788 በቀን 16/04/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 325009 በቀን 27/04/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 334648 በቀን

03/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡

2. የሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 201128 በቀን 25/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**ሄ/መ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**